# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ታኅሣሥ 7 ቀን 2004 ዓ.ም**

**ወያኔ በሚፈጥርባቸው ጫና የሀገሪቱ ባለሀብቶች ስደት ጀመሩ፤**

**ጥቂቶችም እራሳቸውን እያጠፉ መሆኑ ታወቀ፤**

**አንድ የወያኔ የደህንነት ኃላፊም ተገደለ፤**

**ቡና ላኪዎች አድማ ሊመቱ ነው ተባለ፤**

**የነዳጅ ዋጋ በመጨመሩ ኑሮው የከፋ ደረጃ ደረሰ ሲል ህዝቡ አማረረ፤**

ወያኔ የሚያደርስባቸውን ጫና መቋቋም የተሳናቸው ኢትዮጵያዊ ባለሀብቶች ከሀገር እየወጡ ከመሆኑም በላይ በብስጭት እራሳቸውን እያጠፉ እንደሆነ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚደርሰን ጥቆማ ገለፀ።

በሀገሪቱ በተለያዩ የስራ መስክ ተሰማርተው የሚገኙ ባለሀብቶች በወያኔ ባለስልጣናት እና ደህንነቶች በሚደርስባቸው ወከባና እንግልት የተነሳ እየተማረሩ ስራ እስከ ማቆም ከመድረሳቸውም በላይ እየሸሹ ከሀገር እየወጡ መሆኑንም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

ወያኔ በየጊዜው በሚያወጣው አዳዲስ እና አፋኝ ህጎች የተነሳ ባለሀብቶች ስራ መስራት እንዳልቻሉ ቅሬታ ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ጭምር ቢያቀርቡም ምላሽ ከማጣታቸውም በተጨማሪ ጥያቄ በማቅረባቸው ብቻ የተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ናችሁ እየተባሉ ስቃይ እና መከራ.....እንግልት እና ወከባ እየደረሰባቸው በመሰቃየታቸው ብዙዎቹ እየተሰደዱ መሆኑም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

ዛሬ መላ ሀገሪቱዋን የባዕዳን ሀገር ባለሀብቶች ከፋብሪካ እስከ እርሻ......ከግንባታ እስከ ሪል እስቴት ......ከመንገድ ስራ እስከ ህንጻ ስራ ተቀራምተዋት በነጻነት እየሰሩ ባለበት በዚህ ግዜ የሀገሪቱ

ዜጎች ይህንን እድል ከማጣታቸውም በተጨማሪ እድሉን ያገኙትም በደህንነት እና በካድሬዎች ወከባ እየደረሰባቸው ስራቸውን አቁመው እንዲሰደዱ እያደረጉዋቸው መሆኑም ታውቆዋል።

በተለይ በሙስና እራሳቸውን የነከሩት የጉምሩክ እና የሀገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን መስሪያ ቤት ካድሬዎች በሀገሪቱ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ የተሰማሩትን ባለሀብቶች ህጉና መመሪያው ከሚፈቅደው ውጭ ከፍተኛ ጫና እያሳደሩባቸው የጀመሩትን ስራ ጨርሰው እንዳይከውኑ በማድረጋቸው በዙዎቹ ከሀገር ሲሰደዱ ጥቂት የማይባሉት በብስጭት እና በንዴት እራሳቸውን እያጠፉ መሆኑ ታውቆዋል።

ሰሞኑን በአዲስ አበባ ውስጥ በተለያዩ የንግድ ስራ ላይ ተሰማርተው የነበሩ ሁለት ወጣት ባለሀብቶች በጉምሩክ ባለስልጣን እና በሀገር ውስጥ ገቢ ግብር ክፍያ እጅግ ከአቅማቸው በላይ እንዲከፍሉ በመደረጋቸው በመበሳጨት እራሳቸውን ማጥፋታቸው ተገልፆዋል።

በፒያሳ እና በኮልፌ የንግድ ማዕከሎች ውስጥ ከፍተኛ ገንዘብ በማፍሰስ ትልቅ የንግድ ማዕከሎችን እያንቀሳቀሱ የነበሩት ሁለቱ ወጣት ባለሀብቶች በወያኔ ቡድን በደረሰባቸው ከፍተኛ በደል የተነሳ እራሳቸውን በሽጉጥ መግደላቸው ታውቆዋል።

አብርሀም የተባለው የትግራይ ተወላጅ እና ጸጋዬ የተባለው የአዲስ አበባ ተወላጅ ባለሀብቶች በወጣትነታቸው ባፈሩት ገንዘብ ቢሊየነር ለመሆን የበቁ ቢሆንም ከቅርብ ግዜ ወዲህ የተለያዩ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን በገንዘብ እየደገፋችሁ ነው በሚል ባልተረጋገጠ እና ባልተጨበጠ ሁኔታ ሲያንገላቱዋቸው እና ሲያስቃዩዋቸው ከቆዩ በሁዋላ ግብር ከአቅማቸው በላይ እንዲከፍሉና ይህን ተፈጻሚ ካላደረጉ ደግሞ ንብረቶቻቸው እንደሚወረሱ በመነገራቸው በብስጭት ሁለቱም እራሳቸውን መግደላቸው ታውቆዋል።

አብርሀም የተሰኘው ወጣት ባለሀብት ፒያሳ አቅራቢያ በሚገኘው በተለምዶ አፋር ብስኩት ቤት ተብሎ በሚጠራው አጠገብ መኪና ውስጥ ሆኖ በነበረበት ወቅት ከደህንነት ሰዎች ስልክ ተደውሎ ካነጋገረ ጥቂት ደቂቃዎች በሁዋላ እራሱን በሽጉጥ ሊገድል የቻለ ሲሆን ፀጋዬ የተባለውም ወጣት ባለሀብት በበኩሉ ሀገር ውስጥ ገቢ ግብር ለመክፈል ሄዶ የተነገረው እጅግ አስደንጋጭ በመሆኑ ወደ መኖሪያ ቤቱ በመግባት እራሱን እንዳጠፋም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።

ወያኔ የሀገሪቱን ሀብት ለባዕዳን አሳልፎ እየሰጠ እንዲሁም የውጭ ሀገር ባለሀብቶችን እንደ እንቁላል እየተንከባከበ በኢንቨስትመንት ስራ ላይ የተሰማሩትን የሀገሪቱ ዜጎች ግን እያገለለ ከመሆኑም ባሻገር እያንገላታ ስራውን አቋርጠው ከሀገር እንዲወጡ በማድረጉ ቁጥራቸው የበዛ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ወደ መጡበት እየተመለሱ መሆኑንም ከጥቆማው ለመረዳት ተችሎዋል።

በሰው ሀገር ለዓመታት ተንከራትተው ያፈሩትን ሀብት በሀገራቸው ገብተው ለራሳቸውም ለወገኖቻቸውም የስራ እድል ለመፍጠር ሲንቀሳቀሱ የነበሩትን ኢንቨስተሮች የተለያዩ ታፔላዎችን እየለጠፉባቸው ስራ እንዲያቆሙና እንዲሰደዱ በማድረጋቸው ዛሬ እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች እየተሰደዱ ሲሆን ነባር ነጋዴዎችም በፍርሀት ከሀገር ውስጥ ገንዘቦቻቸውን አውጥተው ወደ ተለያዩ ሀገራት እያስቀመጡ መሆኑም ታውቆዋል።

ወያኔ ግን ነባር ነጋዴዎች እና ባለሀብቶች ገንዘቦቻቸውን ወደ ውጭ እንዳያወጡ ለማድረግ በቅርቡ አዲስ መመሪያ በምስጢር ያወጣ ሲሆን በዚሁ መመሪያ መሰረት ገንዘብ ወደ ውጭ ያሸሸ ማንኛ ውም ሰው ከ ገንዘብ መቀጮ እስከ እስራት የሚደነግግ ህግ ማውጣቱም ታውቆዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ከዜጎች ይልቅ ለባዕዳን እያጎበደደ...... ለም መሬቶችን ለእርሻ በሚል እያደለ...... ደኖችን እየመነጠረ ሀገሪቱን ምድረ በዳ እያደረገ...... ባለበት በዚህ ግዜ በእውቀቲና በገንዘቤ ልስራ ብለው እየለመኑ ያሉትን ዜጎች እንዲሰደዱ ከማድረጉም ባሻገር በተቃዋሚነት እየፈረጀ ለእስራት እየዳረጋቸው መገኘቱ አሳዛኝ እና አሳፋሪ ነው ሲሉም በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በንዴት ይገልጻሉ፡፡

ከጥቂት የወያኔ አጎብዳጅ ባለሀብቶች በስተቀር ከውጭም የመጡ ሆነ በሀገር ውስጥ ሆነው ሀብት ያፈሩ ባለሀብቶች ከፍተኛ በደል እና ስቃይ ተሸክመው ያሉበት ወቅት ላይ በመድረሳቸው ቤተሰቦቻቸውን ጭምር ይዘው እየተሰደዱ ሲሆን አሁን ደግሞ በወጣው አዲስ መመሪያ መሰረት ገንዘባቸውን ይዘው እንዳይወጡ በመደረጉ ግራ ተጋብተው እንዳሉም ታውቆዋል፡፡

በቅርቡ በአዲስ አበባ ውስጥ የአከራይ ተከራይ በሚል የንግዱ ማህበረሰብ እርስ በርስ እንዲፋጅ እና እንዲጫረስ አዲስ መመሪያ ቢያወጣም ህዝቡ እርስ በርስ በመነጋገር ችግሩን እየቀረፈ በመሆኑ የተበሳጨት የወያኔ ባለስልጣናት አሁን ደግሞ ሌላ ዘዴ እየቀየሱ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ከዚህ በፊት ከግለሰቦች ላይ ተከራይተው የነበሩትን ወጣቶች እያፈላለጉ ድርሻህ ስለሆነ ጠይቅ በማለት እንደገና ግጭት እንዲቀሰቀስ ውስጥ ውስጡን ከመስራታቸውም በተጨማሪ በይፋ በኤፍ ኤም ራዲዮኖቻቸው ፕሮፓጋንዳ እየነዙ መሆኑን ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

እንደ ሩዋንዳው ቱትሲና ሁቱ ጎሳዎች የንግዱን ህብረተሰብ ሊያፋጁት እቅድ የነደፉት የወያኔ ባለስልጣናት እቅዳቸው ሳይሰራ መና በመቅረቱ አሁን ደግሞ ሌላ ዘዴ ቅስቀሳ በመስራት ላይ መሆናቸው እጅግ የሚያሳፍር ተግባር መሆኑን የንግዱ ህብረተሰብ እየገለፀ ይገኛል፡፡

በሌላ ዜና በህዝብ ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈጽም የነበረ አንድ የወያኔ የደህንነት ባለስልጣን ባለፈው ሳምንት ውስጥ በገጀራ አንገቱ ተቆርጦ ተገድሎ መገኘቱ ታወቀ፡፡

የለገደንቢ የወርቅ ማዕድን ደህንነት ኃላፊ የነበረው ይሄው ግለሰብ በአካባቢው ህዝብ ላይ ይህ ቀረሽ የማይባል ግፍ እና መከራ ሲሰራበት የነበረ ሲሆን ከዚህ በፊት የሀገራችን ሀብት የሆነው ወርቅ ወደ ውጭ አይጫንም ብለው የአካባቢው ነዋሪዎች ተቃውሞ ባሰሙበት ወቅት ሰራዊት ወደ አካባቢው ሰርጎ እንዲገባና በህዝቡ ላይ የእሩምታ ተኩስ እንዲከፍት አድርጎ ከአምስት ሰዎች በላይ ያስገደለ እንደነበረም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል፡፡

የህዝብ ሀብት የሆነውን ወርቅ ለሼህ አላሙዲን የሸጠው ወያኔ የአካባቢው ህዝብ እንዳያውቅ እና ተቃውሞ እንዳያሰማ አፈና እንዲፈጽም በምስጢር ተመድቦ የነበረው የደህንነት ኃላፊ ባለፈው ሳምንት በቆንጨራ ታርዶ ተጥሎ መገኘቱ የአካባቢው መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱም ታውቆዋል፡፡

በህዝቡ ላይ ከፍተኛ በደል ሲፈጽም እና ሲያስፈጽም የነበረው ይሄው ግለሰብ ባልታወቁ ሰዎች አንገቱን በቆንጨራ ታርዶ ከተጣለ በሁዋላ በምትኩ ከበረሀ የመጣው እና ጡረታ የወጣው የወያኔ ጄኔራል እንደተሾመም ለማወቅ ተችሎዋል::

ለብዙ ዓመታት በዚሁ ኃላፊነት ቦታ ላይ ተቀምጦ ሲሰራ የነበረው ይሄው ግለሰብ በህዝቡ ላይ በሚፈጽማቸው ተደጋጋሚ ወንጀሎች በሀገር ሽማግሌ ጭምር ቢመከርም አሻፈረኝ በማለቱ ማንነታቸው ያልታወቁ ግለሰቦች ጨለማን ተገን አድርገው እርምጃ የወሰዱበት መሆኑን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በየቀኑ በኪሎ እየተመዘነ ከሚታፈሰው ወርቅ ገቢ አንዳችም ነገር ተጠቃሚ ያልሆኑት የአካባቢው ነዋሪዎች ትምህርት ቤት እና ጤና ጣቢያ ይሰራልን ብለው ከዛሬ ስድስት ወር በፊት ተቃውሞ በማሰማት የወረዳውን ባለስልጣኖች እያሳደደ ዱር ለዱር ሲያባርር በነበረበት ወቅት ድንገት ተወርዋሪ ጦር እንዲመጣና በእሩምታ ተኩስ እንዲፈጃቸው ትዕዛዝ የሰጣቸው ይሄው ግለሰብ እንደነበረም የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል::

ሰሞኑን ይህ የደህንነት ኃላፊ ከተገደለ በምትኩ የተተከው ጡረታ የወጣ የወያኔ ጄኔራል ህዝቡ አመፅ አንስቶ ችግር ሊፈጥር ይችላል በሚል ፍርሀት ወደ ቦታው ሳይሄድ እዚሁ አዲስ አበባ ላይ ቢሮ ከፍቶ እንደተቀመጠም ለማወቅ ተችሎዋል::

ከዚህ በፊት በዚሁ በለገደንቢ ወርቅ ምርት ጥቅም ሳቢያ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ሚስት አዜብ መስፍን እና ሼህ አላሙዲን ግጭት ፈጥረው ይሄንኑ ችግር አዛውንቱ ስብሀት ነጋ በሽምግልና እንደጨረሰው ዘግበን የነበረ ቢሆንም አሁንም ለግዜው ጋብ ይበል እንጂ ውስጥ ውስጡን ሽኩቻው መኖሩንም ለድርጅቱ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል::

ቀድሞ የነበረው የለገደንቢ የወርቅ ማምረቻ ቦታ አልቆ በአሁኑ ሰዓት በድጋሚ 50 ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው መሬት እዚያው የተረከበ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በጋምቤላ ክልል ውስጥም በተመሳሳይ ከ50 ኪሎ ሜትር በላይ ስፋት ያለው መሬት መረከቡንና የወርቅ ማውጣት ስራውን እየሰራ መሆኑ ታውቆዋል::

ህዝብ በርሀብ እንደ ቆሎ እየረገፈ ባለበት በዚህ ግዜ በተለይ የማዕድኑ የሚወጣበት ዞን ህዝብ በችጋር እየሞተ መሆኑን የሚያውቀው ይሄው ግለሰብ አንዳችም እርዳታ ሳይሰጥ ይልቁንም የወያኔን ስርዓት እድሜ ለማራዘም መሳሪያ መግዣና የደህንነት ኃይሉን ማጠናከሪያ በምስጢር እና በይፋ ገንዘብ መስጠቱ የሚያሳዝን ድርጊት ነው ሲሉም የአካባቢው ነዋሪዎች በቁጭት ይገልፃሉ::

በመጨረሻም በዓለም ላይ የነዳጅ ዋጋ ቀንሶ እያለ የወያኔ ቡድን ሰሞኑን እንደገና አዲስ የዋጋ ጭማሪ ማድረጉ ተፈጥሮ የነበረው የኑሮ ውድነት እንዲባባስ እና ህዝቡም ለከፋ ችግር እንዲዳረግ መደረጉ ታወቀ::

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን ባወጣው የዋጋ ጭማሪ ታሪፍ በቤንዚን እና በናፍታ ላይ ከ1ብር በላይ በመጨመር በኑሮ ውድነቱ ከፍተኛ ጫና ከመፍጠሩም በላይ ህዝቡ ኑሮው ከአቅሙ ላይ እንዲሆንበት ማድረጉ ታውቆዋል።

በአሁኑ ሰዓት የዓለም ነዳጅ ዋጋ እየቀነሰ አልፎ አልፎም ባለበት እየሄደ ባለበት በዚህ ግዜ የወያኔ ቡድን በማን አለብኝነት ብቻ የህዝቡን አቅም ሳያገናዝብ ጭማሪ በማድረጉ በእህልና በጥራጥሬ እንዲሁም በትራንስፖርቶች ላይ ዋጋ ጭማሪ መደረጉ ታውቆዋል።

በአሁኑ ሰዓት በነዳጅ ዋጋው ላይ ጭማሪ የተደረገው ከዚህ ቀደም በውድ ዋጋ ገዝተን ያስቀመጥነው በመሆኑ ነው ያለው የወያኔ ቡድን ከአራት እና ከዚያም ወር በፊት የአንድ በርሜል ድፍድፍ ነዳጅ ዋጋ ከ100 ዶላር በላይ ሳይዘል ተገዝቶ የተቀመጠ መሆኑ እየታወቀ ዛሬ በዓለም ላይ ዋጋው በተረጋጋበት ወቅት ድንገት የዋጋ ጭማሪ መደረጉ የበህዝቡ ኑሮ ላይ ቤንዚን ማርከፍከፍ መሆኑንም ነዋሪዎች በብስጭት ይገልፃሉ።

ይሄንኑ የነዳጅ ዋጋ ጭማሪን ተከትሎ ሰሞኑን በትራንስፖርት ዋጋ ላይ የተጨመረ ሲሆን በእህሎች እና በሌሎች ሸቀጦች ላይም ጭማሪ ማሳየቱ ታውቆዋል።

ከሀገሪቱ ህዝብ ይልቅ ባዕዳን የሚበልጡበት የወያኔው ቡድን ዛሬ የኑሮ ውድነቱ ከህዝቡ አቅም በላይ ባናጠረበት በዚህ ግዜ ገበያውንና መሰል ጉዳዮችን ከማረጋጋት ይልቅ ሆን ብሎ እንዲባባስ እና የበለጠ እንዲጎር በማድረጉ ዜጎች ለከፋ ችግር ተዳርገው ሲገኙ በአንጻሩ ደግሞ ለቻይና እና ለሌሎች የውጭ ሀገር ዜጎች ኑሮዋቸውን በማመቻቸት የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ እያደረገ መሆኑም ታውቆዋል።

ዛሬ አንድ ቻይናዊ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በዶላር እየተከፈለው በቀን ሰራተኛ ጭምር ተሰማርቶ የሚገኝ ሲሆን ከዚህም በላይ ግብር እና ታክስ ሳይቆረጥበት ከዜጋው በላይ ተንደላቆ ሲኖር የሀገሪቱ ህዝቦች ግን በችጋር እና በኑሮ ውድነት እየተጠበሱ ባለበት ሰዓት ይባስ ብለው በነዳጅ ላይ ጭማሪ ማድረጋቸው እጅግ ከፍተኛ የህዝብ ንቀትና ጥላቻ እንዳለባቸው በግልጽ ያሳየ ነው ሲሉም ነዋሪዎች በምሬት ይገልጻሉ።

ህዝቡ የዕለት ጉርሱን መሸፈን አቅቶት እየተንገዳገደ ባለበት በዚህ ግዜ ወያኔ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ሲል ብቻ የተለያዩ አዳዲስ ጅምር ፕሮጀክቶችን እየከፈተ ከህዝቡ ላይ በግዳጅ እየነጠቀ ባለበት በዚህ ግዜ በነዳጅ ዋጋው ላይ በመጨመር ኑሮው እጅግ እንዲጎር በማድረጉ ህዝቡ በየቤቱ እያነባ ይገኛል።